የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አንደኛ ዓመት ቁጥር ፪
አዲስ አበባ — ነሐሴ ፲፮ ቀን ፲፱፻፹፯

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

1st Year No. 2
ADDIS ABABA 22nd August 1995

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪/፲፱፻፹፯ ዓ.ም.
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
መንግሥት መመሥረቱን ለማስታወቅ የወጣ
አዋጅ ........................................................ ገጽ ፴፱

CONTENTS

Proclamation No. 2/1995
Declaration of the establishment of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Procalamation ............................................ Page 39.

## አዋጅ ቁጥር ፪/፲፱፻፹፯

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መመሥረቱን ለማስታወቅ የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መርጠው በላኳቸው ተወካዮቻቸው አማካይነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥትን ያፀደቁ በመሆኑ ፤

በፀደቀው ሕገ መንግሥት በተደነገገው መሠረት የፌዴራሉ መንግሥት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት ምርጫና ውክልና ተከናውኖ የፌዴሬሽኑ መሥራች ጉባዔ የተካሄደ በመሆኑ ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ፤

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት መመሥረቱን ለማስታወቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፪/፲፱፻፹፯» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· የፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መመሥረት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ከነሐሴ ፲፭ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ·ም· ጀምሮ ተመሥርቷል ።

፫· ሥልጣን ስለመረከብ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከነሐሴ ፲፭ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ·ም· ጀምሮ የመንግሥት ሥልጣንን ከሽግግሩ መንግሥት ተረክቧል ።

## PROCLAMATION NO. 2/1995

## A PROCLAMATION TO DECLARE THE ESTABLISHMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

WHEREAS, the Nations, Nationalities and Peoples of Ethiopia have, through their elected Representatives, ratified the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

WHEREAS, the Founding Assembly of the Federation has been convened subsequent to the election and delegation, pursuant to the provisions of the Constitution, of Deputies to the House of Peoples' Representatives and to the House of the Federation of the Federal Government;

NOW THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

*1. Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Declaration of the Establishment of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 2/1995''.

*2. Establishment of the Federal Democratic Republic*

The Federal Democratic Republic of Ethiopia is established as of the 21st day of August, 1995.

*3. Transfer of Power*

The House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, has state power transferred to it from the Transitional Government as of the 21st day of August, 1995.

፬· <u>ስለተሻሩ ሕጎች</u>

የሚከተሉት በዚህ አዋጅ ተሽረዋል ፤

፩· የሽግግሩ ወቅት ቻርተር፤

፪· የፕሬዚዳንቱን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፩/፲፱፻፹፫ ።

፭· <u>ስለነባር ሕጎች ተፈጻሚነት</u>

በሥራ ላይ ያለ ማንኛውም ሕግ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ጋር እስካልተቃረነ ድረስ ተፈጻሚነቱ ይቀጥላል ።

፮· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከነሐሴ ፳፪ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ·ም· ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፪ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ·ም·

(ዶ/ር) ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

4. *Repeals*

The following are hereby repealed:

1. The Transitional Period Charter;
2. The Definition of the Powers and Functions of the President Proclamation No. 1/1991.

5. *Application of Prior Laws*

All prior laws shall continue to apply unless they are inconsistent with the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

6. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 22nd day of August, 1995.

Done at Addis Ababa, this 22nd day of August, 1995

*NEGASSO GIDADA (DR.)*
*PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ ።
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE